# የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ ጉብኝቶች ወይም ወረራዎች ("Raids")፡ እንዴት እንደሚሰሩ

የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ ጉብኝቶች ያለማስጠንቀቂያ ሊከሰቱ ይችላሉ። ከሁሉ ይልቅ በጣም የተለመዱ ጉዳዮች ህጋዊ ሰነዶችን መመርመርን ያካትታሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች የስደተኛ መኮንኖች ማስረጃን እየፈለጉ ነው ወይም የተወሰኑ ግለሰቦችን ይፈልጋሉ። ለመዘጋጀት እና ለስደት ማስፈጸሚያ ጉብኝቶች እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ ለማወቅ ይህንን መመሪያ ይጠቀሙ።

## የሀገር ውስጥ ደህንነት መምሪያ የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ የሚከተሉትን ያካትታል

- **የሀገር ውስጥ ደህንነት ምርመራዎች (HSI)** የአሰሪዎችን ቅጽ I-9 (የቅጥር ብቃት ማረጋገጫ) እና ተሟልተው እንደሆን ሌሎች ሰነዶችን ይመለከታል።
- **የኢሚግሬሽን እና የጉምሩክ ማስፈጸሚያ (ICE)** የኢሚግሬሽን ህግን ያስፈጽማል እናም ዜግነት የሌላቸውን ማሰር እና ማባረር (ከሀገር ማስወጣት) ይችላል። የ ICE ወኪሎች ፖሊሶች አይደሉም ነገር ግን ሽጉጥ ሊይዙ ይችላሉ እና "ፖሊስ" ወይም ከላዩ "ERO" (የማስፈጸም እና የማስወገድ ክንውኖች) የሚሉ ልብሶችን ይለብሳሉ።
- **የጉምሩክ እና የድንበር ጥበቃ (CBP)** በድንበር ላይ ማን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ሊገባ እንደሚችል ለመወሰን እና በመሬት ወይም በባህር ድንበር እስከ 100 ማይል ርቀት መካከል ያሉ ሰዎችን ድንበር ጠባቂ ተወካይ ድርጅቶችን በመጠቀም የፍተሻ ነጥቦችን ማዘጋጀት ወይም መጠይቅ ይችላል።
- **የዩ ኤስ ዜግነት እና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች (USCIS)** ከስራ ጋር የተዛመዱ የኢሚግሬሽን አቅራቢ/የገንዘብ ደጋፊ ይመረምራል እና የስራ ጣቢያዎችን መጎብኘት ይችላል።

## ከማንኛቸውም የICE ወይም ሌላ የኢሚግሬሽን መኮንን ጉብኝት በፊት

- ቅጽ I-9 እና ሌሎች የኢሚግሬሽን ወረቀቶች ተሞልተው እና ትክክለኛ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ውስጠኛው ቅጽ I-9ን ኦዲት ያድርጉ እና ስህተቶችን ያስተካክሉ።
- ለኢሚግሬሽን መኮንኖች አንድን ሰው ወይም መምሪያ (እንደ የሰብአዊ ሀብቶች/ የሰራተኛ አስተዳደር ወይም ህጋዊ ክፍል ያሉ) የመገናኛ ነጥብ አድርጎ መሰየም።
- የኢሚግሬሽን መኮንኖች ያለፈቃድ ወይም የፍርድ ቤት ማዘዣ እንዳይገቡ በታዎችን እንደ “የግል” ምልክት ያድርጉ።
- ከሶሻል ሴኩሪቲ አስተዳደር "No-Match" የሚል ደብዳቤ ከደረሰዎት፣ እንዴት ለማስተካከል እንደሚሞክሩ ይመዝግቡ።

## የICE ወይም ሌላ የኢሚግሬሽን ፖሊሶች ከመጡ

- ተረጋጉ። ስሞችን ለማስታወስ ይሞክሩ እና እየሆነ ያለውን ነገር ትኩረት መስጠት።
- ህዝባዊ አካባቢዎች ወደ ሆኑ በታዎች እንዲገቡ መፍቀድ። ማንኛውም ሰው፣ የICE ተወካይ ተጠሪዎችን ጨምሮ፣ ወደ እርስዎ ንግድ ህዝባዊ አካባቢዎች ያለፍቃድ መግባት ይችላሉ። ህዝባዊ አካባቢዎች የማስተናገጃ አካባቢ፣ መቀበያ አካባቢ፣ የፊት ቢሮ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እና ለሕዝብ ተደራሽ የሆኑ በታዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የኃላፊነት ቃል፡- ይህ ሰነድ ለደንበኞቻችን እና ለጓደኞቻችን የቅርብ ጊዜ የህግ እድገቶችን ለማሳወቅ የDavis Wright Tremaine LLP, DWT -com ህትመት ነው። የሕግ ምክር አይደለም። ይህ ሰነድ በሲያትል ከተማ ተተርጉሟል፤ ነገር ግን፣ ይዘቱ የተደራጀው በከተማው አይደለም። መረጃው ከሥር መሠረቱ የመጣው ከDavis Wright Tremaine LLP ድርጅት ነው።

Davis Wright Tremaine LLP Immigration Group
dianebutler@dwt.com | 206-757-8354 | meganvogel@dwt.com | 206-757-8258

ወኪሎቹን ለመታወቂያ፣ በኋላ ሊደውሉለት ስልክ ቁጥር እና ለምን እንደመጡ የሚገልጽ ማስታወሻ መጠየቅ። የሰባዊ ሀብቶችን፣ ሥራ አስኪያጅን፣ የኩባንያውን ጠበቃ፣ ወይም ልዩ ተጠሪ ሆኖ የተሰየመውን ያነጋግሩ።

## የወረቀት ሥራ ዓይነቶች

- **የፍተሻ/ የምርመራ ማስታወቂያ** — ይህ በ 3 የስራ ቀናት ውስጥ የእርስዎን ቅጽ I-9 ለማጋራት ከ ICE ወይም የአገር ደህንነት የሚቀርብ ጥያቄ ነው። ምላሽ ከመስጠትዎ በፊት አንድ ጠበቃ ማነጋገር።
- **የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ የፍርድ ቤት መጥሪያ** — ይህ ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰነዶችን ከቅጽ I-9 ጋር ይጠይቃል።
- **የፍርድ ቤት እስራት ወይም የፍተሻ ማዘዣ**— ይህ ማዘዣ የተፈረመው በፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛ ወይም ዳኛ ነው። የ ICE ወኪሎች ወደ ግል በታዎች እንዲገቡ ወይም ሰነዶችን እንዲወስዱ ሊፈቅድላቸው ይችላል። ማዘዣውን ያንብቡ። ህጋዊነት ያለው መሆኑን ያረጋግጡ እና ከማዘዣው ውጭ ላለው ማንኛውም ነገር አይስማሙበት።
- **አስተዳደራዊ ማዘዣ** — ይህ አብዛኛውን ጊዜ "የሃገር ውስጥ ደህንነት መምሪያ" ወይም "ኢሚግሬሽን እና ጉምሩክ ማስፈጸሚያ" የሚል አለው እና ቅጽ I-200 ወይም ቅጽ I-205 ይሆናል። አሠሪው/ ቀጣሪው በዳኛ የተፈረመ ወይም ከፍርድ ቤት በወጣ የመጥሪያ ህጋዊ ማዘዣ ከሌለ “መስማማት አልችልም፣ መስማማት አልፈቅድም” ማለት አለበት። ICE የአንድ ሰራተኛ ስም በላዩ ላይ ያለበት አስተዳደራዊ ማዘዣ ካሳየ:-
    - ሰራተኛው በዚያ ቀን እየሰራ እንደሆነ እርስዎ መናገር **የለብዎትም**።
    - እርስዎ የ ICE ወኪሎችን በማዘዣው ላይ ወደተጠቀሰው ሰራተኛ መውሰድ **የለብዎትም**።
- **በ ICE የተያዙ ዕቃዎች ደረሰኝ** — መዝገቦች ተይዘው ከሆነ፣ የወሰዱትን ነገሮች ለመከታተል እንዲቻል ICE ለኩባንያው ደረሰኝ መስጠት ይኖርባቸዋል።

## በጉብኝቱ ወቅት ከሠራተኞች ጋር የሚደረግ የግንኙነት ልውውጥ

- ሰራተኞች እንዲረጋጉ እና መሸሽ **እንዳያደርጉ/ እንዳይሮጡ** አሳስቧቸው። የ ICE ወኪሎች የሚሸሹ ሰዎችን ሊያሳድዱ/ አባርረው መያዝ እና የኢሚግሬሽን ህጎችን ጥሰዋል ብለው የሚጠረጥሯቸውን ሰዎች ማሰር ይችላሉ።
- የ ICE ወኪሎችን እንዲሰሩ በሕግ የተፈቀደላቸውን መፈጸም ጣልቃ እስካልገቡ ድረስ እርስዎ ቪዲዮ ማንሳት ወይም መቅዳት ይችላሉ።
- በፍርድ ሥርዐት ማዘዣ፣ ICE ስልኮችን፣ የእጅ ኮምፑተሮችን/ ላፕቶፖችን ወዘተ መሳሪያዎቹን ሳይወስዱ ፎቶ ማንሳት፣ ወይም መረጃውን ሊቃኙ፣ ወይም ውርስ ማድረግ ይችላሉ።
- ICE ማንንም እንዲያቆሙ፣ አቁመው እንዲጠይቁ ወይም እንዲያስሩ፣ ወደፈለጉበት ቦታ እንዲሄዱ ወይም የፈለጋቸውን እንዲወስዱ ፈቃድ **አለመስጠት**።
- ከICE ወኪሎች ጋር የሰዎችን የኢሚግሬሽን ሁኔታ/ ደረጃ ወይም የመጡበትን ሀገር በመጋራት ወኪሎችን **አይረዷቸው**።
- ሁሉም ሰራተኞች ሲጠየቁ ዝም የማለት እና ጠበቃ የመጠየቅ መብት አላቸው። ሰራተኞች ማንኛቸውንም መታወቂያ ወይም ወረቀቶችን ለ ICE እንዲያስረክቡ አይጠበቅባቸውም።
- ሰራተኞች ለ ICE የሚሰጡት ማንኛቸውም መረጃ በኋላ ላይ በነሱ (በሠራተኞቹ) ላይ መጠቀም ይቻላል።
- ማንኛውም የታሰረ ሰው አንድ ጠበቃ እና "በቂ ምክንያት የማሳያ ችሎት" መጠየቅ አለበት።

የኃላፊነት ቃል፡- ይህ ሰነድ ለደንበኞቻችን እና ለጓደኞቻችን የቅርብ ጊዜ የህግ እድገቶችን ለማሳወቅ የDavis Wright Tremaine LLP, DWT -com ህትመት ነው። የሕግ ምክር አይደለም። ይህ ሰነድ በሲያትል ከተማ ተተርጉሟል፤ ነገር ግን፣ ይዘቱ የተደራጀው በከተማው አይደለም። መረጃው ከሥር መሠረቱ የመጣው ከDavis Wright Tremaine LLP ድርጅት ነው።

Davis Wright Tremaine LLP Immigration Group
dianebutler@dwt.com | 206-757-8354 | meganvogel@dwt.com | 206-757-8258

## ከጉብኝቱ በኋላ ወዲያውኑ

- የመጡ መኮንኖች ከሄዱ በኋላ እነዚህን ነገሮች ይፃፉ ወይም ይቅዱ:-
  - ስንት የ ICE ወኪሎች (ውስጥም ሆነ ውጪ) ተገኝተዋል? ስማቸው ማን ማን ነበር?
  - የወኪሎቹ አለባበስ እንዴት ነበር? የታጠቁት እንዴት ነበር?
  - ወኪሎቹ እርስዎን ወይም የእርስዎን ሰራተኞች መንቀሳቀስ ወይም መውጣት እንደማትችሉ እርስዎ እንዲያምኑ አድርገዋል?
  - ወኪሎቹ ማንንም አስፈራርተው ወይስ አንገላተው ነበር? መልሱ አዎ ከሆነ፣ እንዴት?
- ICE ማንንም የሚያስሩ ከሆነ፣ የ ICE ወኪሎች ሰዎችን ወዴት እየወሰዱ እንዳሉ ይጠይቁ።
- የቅጽ I-9 ምርመራ/ ፍተሻ ካለ፣ ሰነዶቹን ያዘጋጁ። እርስዎ መዝገቦቹን ለማስረከብ ከ3 ቀናት በላይ እንዲሆን መጠየቅ ይችላሉ።

የኃላፊነት ቃል፡- ይህ ሰነድ ለደንበኞቻችን እና ለጓደኞቻችን የቅርብ ጊዜ የህግ እድገቶችን ለማሳወቅ የDavis Wright Tremaine LLP, DWT -com ህትመት ነው። የሕግ ምክር አይደለም። ይህ ሰነድ በሲያትል ከተማ ተተርጉሟል፤ ነገር ግን፣ ይዘቱ የተደራጀው በከተማው አይደለም። መረጃው ከሥር መሠረቱ የመጣው ከDavis Wright Tremaine LLP ድርጅት ነው።

Davis Wright Tremaine LLP Immigration Group
dianebutler@dwt.com | 206-757-8354 | meganvogel@dwt.com | 206-757-8258